አምባሳደርዋ በኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ያደረጉት ንግግር

ማክሰኞ ነሐሴ 17 ቀን 1997 ዓ.ም

እንደምን ዋላችሁ:: የኢትዮጵያ ንገድ ምክር ቤት የክብር እንግዳ በመሆን በድጋሜ እዚህ በመገኘቴ ታላቅ ደስታ ይሰማኛል:: ኢትዮጵያ ውስጥ በቆየሁበት ጊዜ ለተደረገልኝ መስተንግዶና በከፍተኛ ፍላጐት የመርህ ግብራችን ተባባሪ በመሆናችሁ አቶ አንዱአለምንና መላውን የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት አባላት ለማመስገን እፈልጋለሁ::

በዚህ ሀገር የነበረኝ የሶስት አመት የስራ ተልዕኮዬ የሚያበቃ በመሆኑ ይህ በኢትዮጵያ የመጨረሻ ንግግሬ ይሆናል::

ዛሬ ምን መናገር እንዳለብኝ ሳሰላስል አእምሮዬና ልቤ ወደአደግሁበት አትላንታ-ጆርጅያ ተመልሼ ስር መሰረቴን እንድዳስስ ገፋፉኝ:: እንደዲፕሎማትና ኋላም እንደ አምባሳደር በቆየሁባቸው ዓመታት እጅግ ጠቃሚ የሆኑትን የልጅነት ጊዜዬን ደጋግሜ አስታውሳለሁ:: ከቤተሰቤ የአፍሪካ አሜሪካውያንን ባህል እንዳደንቅ እውቀት ገብይቻለሁ:: ይህም ለስራ ተነሳስቼ ተልዕኮዬን በአግባቡ እንድወጣ ጥንካሬን አላብሶኛል:: በልጅነቴ የኔግሮ መንፈሳዊ መዝሙር እየተባለ የሚጠራውን ያኔም ሆነ አሁን እወደዋለሁ:: በተለይ በአፍሪካ አሜሪካዊው አዶልፈስ ሄይልስቶርክ የተቀናበረው «Done Made My Vow» የተሰኘው መዝሙር የተለየ ትርጉም ይሰጠኛል:: ይህን መዝሙር ያስተማረኝ አጐቴ ብራዚያል ዴናርድ ሲሆን እሱም የተከበረ የሙዚቃ አዘጋጅና አቀናባሪ መሆኑን ስናገር በኩራት ነው:: በዚህ መዝሙር ግጥሞችና ስሜት ኮርኳሪ መልዕክቶች ተመስጫለሁ::

አጐቴ እንደነገረኝ የእኛ ወላጆች ትውልድ ከዚህ ትምህርት ቀስመው የመንፈስ ብርታትን በማግኘት በአስቸጋሪ ወቅቶች ውስጥ ለማለፍ ይችሉ ነበር:: እነሱ ለኛ የሚያስተላልፉት አጠቃላይ መልዕክት የቱንም ያህል አስቸጋሪ ሁኔታ ቢገጥመን በህይወታችን የተነሳንበትን ዓላማ በዕናት ግብ መምታት አለበት ብለው ነው:: እንደአፍሪካ አሜሪካዊነቴ የእኔ የህይወት ልምድ ከዚህ መንፈስና ባህል ጋር በስሜት ተሳስሯል:: አሁንም የምመራው ሀገሬ በነበርኩ ጊዜ ከቤተሰቤ፣ ከቤተክርስቲያን፣ ከትምህርት ቤትና ከማህበረሰቡ ውስጥ በቀሰምኳቸው ነው:: እስከአሁንም «Done Made My Vow» የሚለው ግጥም መመሪያዬ ነው::

«Done Made My Vow to the lord;
«እሄዳለሁ ፣ ፍፃሜውንም ለማየት እጓዛለሁ
ቶይል ስሜ ነው፣ እናቴ ጥንካሬዬ
ለወደፊቱ ስኬት ፣ ግቤ ኩራት ነው »

እ.ኤ.አ በ1960ዎቹ እኔ ህፃን ልጅ ነበርሁ:: በአሜሪካ ያ ትውልድ በርካታ ህፃናት የተወለዱበት ዘመን ተብሎ ይታወቃል:: እነዚህ በርካታ ህፃናት ብሩህ ተስፋ ከፈነጠቀበት ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ማግስት የተወለዱ ናቸው:: ይህ ትውልድ ለአለም ያበረከተው አንድ ነገር ቢኖር በበጐ ለውጥ በጥልቀት ማመኑ ነው:: ዛሬ እዚህ ያላችሁት የእናንተ ልጆችም ጭምር በመጠንም በአስተዋፅኦም ከዚያ ትውልድ ይበልጥ ለሀገራችሁና ለአለም ጭምር ለውጥ ለማምጣት መልካም አጋጣሚ አላችሁ::

እናንተ ይህ በጐ ገፅታ እንዲመጣ ሀይል ለመሆን ከመወሰን ባሻገር ይህ ለውጥ ምን ሊሆን እንደሚችል መቀየስም ይጠበቅባችኋል:: ከእናንተ ጀርባ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ የቤተሰቦቻችሁ ተስፋና የበፊቱ ትውልድ ያበረከተላችሁ ቅሪት አለ:: እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ሴት ወይም ወንድ የበጐውን ጅምር ፍፃሜ ለማየትም ኃላፊነት አለባችሁ::

ፍፃሜው ምን ይሆናል ብዬ ሳሰላስል ለጊዜው በሴቶች ላይ ትኩረት ማድረግን መረጥሁ። በነበርኩባቸው በርካታ የአለም ሀገሮች ውስጥ ሴቶች የለውጥ ሀይል መሆናቸውን አይቻለሁ። ለምን ብትሉኝ ፤ ምክንያቱ ሴቶች ከራሳቸውና ከግለኝነት ባሻገር ስለሚያስቡ ነው። ሴቶች ለልጆቻቸው፣ ለቀጣዩ ትውልድና ቤተሰቦቻቸው ያስባሉ። ለሁሉም ህብረተሰብ የሚጠቅም ለውጥ ለማምጣት ፈቃደኞች ናቸው። ሴቶች ሁሉንም ያካትታሉ። እነሱ ራሳቸው ተጠቃሚ ባይሆኑም ለውጥን በሰፊው ህብረተሰቡ ውስጥ ለማስረፅ ይሰራሉ። ለዚህም ምክንያቱ በአብዛኛው ሴቶች በህብረተሰቡ ውስጥ የተጠቃሚነት ስፍራ ስለሌላቸው ለራሳቸው ጥቅም ብለው አጥብበው አይመለከቱም ብዬ ስለምረዳ ነው። ሴቶች ሁሉንም በማካተት ለውጥን ለማምጣት ከሌሎች ጋር ለመስራት አይቸገሩም። እሷ አፍሪካዊት ወይም አፍሪካ አሜሪካዊት ብትሆን ስለ ጥቁር ህዝብ ግንዛቤ እንዲዳብርና የሰው ልጅ ደግነትና ርህሩህነት ጐልቶ እንዲወጣ ከመስራት የሚያግዳት የለም። የህግ አውጪነት ስፍራ ከያዘችም ስልጣን ሊፈጥር የሚችለውን ትዕቢት ለማስወገድ አቅም ይኖራታል፤ የዚህ ትዕቢት ተጐጂ ናትና። ሴት ልጅ ያለችበትን ልዩ ስፍራ የምታውቅ፣ በምትሰራው የምትደሰትና ሌሎችንም በመልካም አቀባበል ወደ ብርሃን የምትመራ ናት።

በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ የሴት አምባሳደር እንደመሆኔ የኢትዮጵያ ሴቶች በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ብልፅግናን ለማምጣት በርትተው እንደሚሠሩ ተገንዝቤአለሁ። የዚህ ጥረታቸውን ፍፃሜ ለማየት የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ አደንቃለሁ። ከዚህ ሌላ በጐ ለውጥን የሚያመለክት ምን አለ?

እነዚህ ሴቶችና ወንዶች በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመንና በበፊተኞቹ ምዕተ አመታት ጭምር በስልጣን ላይ ያሉት በእንዴት ያለ ሁኔታ ኃላፊነታቸውን ስልጣን ለሌላቸው ሊያጋሩ ይችላሉ? የሚለውን አቢይ የህብረተሰብ ችግር እየተረዱ ይገኛሉ። በኢትዮጵያ በአብዛኛው የመድብለ ፓርቲ ፖለቲካ እንዲኖርና ኢኮኖሚው ለቀቅ ያለ እንዲሆን ሰፊ ስምምነት አለ። የኢኮኖሚ እድገትን ለማስመዝገብ የመንግስት ቁጥጥር መላላት ይኖርበታል። እኔ እንደማምነው ብዙዎች ኢትዮጵያዊያን የሚፈልጉት በህገ መንግስቱ ውስጥ የሰፈሩት መብቶችና ድንጋጌዎች እንዲከበሩላቸው ነው። እንደገናም በእኔ እምነት ብዙ ኢትዮጵያዊያን መገናኛ ብዙሃን ሁሉንም እንዲያገለግሉ ይፈልጋሉ። አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ በዲሞክራሲ የተመረጠ መንግስት እንዲመሰረትለት ይፈልጋል ብዬ አምናለሁ። መንግስት የግለሰብ መብትን ማክበር አለበት። በከፍተኛ ጥረት የተገኙት መብቶችም መጠበቅ ይኖርባቸዋል።

አንዳንድ ኢትዮጵያዊያን የነገሩኝን ላውጋችሁ። እንደ ወላጅነታቸው ልጆቻቸው እነሱ እንደነበሩበት ዘመን በጦርነትና ብጥብጥ ውስጥ እንዲያልፉ አይፈልጉም። እንደነገሩኝ ከሆነ ፖለቲከኞች እርስ በርስ መከባበር ፣ በትህትና መነጋገርና ለህዝብ ለሚጠቅሙ ጉዳዮች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። አንዱ ሌላኛውን ለማጥፋት መስራት አይኖርበትም። እነዚህ ሰዎች እንደገሩኝ የኢትዮጵያ ህዝብ በታሪኩ እርስ በርስ መቻቻልንና አብሮ መኖርን አላዳበረም። ግን ለልጆቻቸውና ለሀገሪቱ መሪዎች እነዚህ ልማዶች እንዲዳብሩለት ይፈልጋል። በተጨማሪም እነዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫውን ውጤት በመቀበል ፓርላማ እንዲገቡና በስርአቱ ውስጥ እንዲሰሩ እንደሚፈልጉ ነግረውኛል። ህዝቡ የዲሞክራሲ ተቋማትንና ህገ መንግስቱን ያከብራል። የፖለቲካ ፓርቲዎችም በተመሳሳይ እነዚህን ተቋማት እንዲያከብሩለት ይፈልጋል። ሰላምንና ብልህ መሪዎችንም ይሻል።

ይህን በግልፅ ለማስቀመጥ አንድ አጭር ታሪክ ልንገራችሁ። ይህን ያነበብሁት የኖቬል ሎሪት እና የፑሊትዘር አሸናፊ ከሆኑት ቶኒ ሞሪሰን ተደናቂ ንግግር ላይ ነው። እሳቸው የታወቁ አፍሪካዊ ፀሐፊ ናቸው። ፅሁፉ እንደሚለው አንድ በእድሜ የገፉ ባልቴት አይነስውር ነበሩ። እኚህ ሴት አዋቂ ስለነበሩ በህብረተሰቡ ዘንድ ይከበራሉ። ያም ቢሆን የሚንቋቸው፣ በአይነስውርነታቸው ዝቅ አድርገው የሚመለከቷቸውና ሊያስቁባቸው የሚፈልጉ ሰዎች መኖራቸው አልቀረም። በአንድ ወቅት ሶስት ወጣቶች ጥያቄ ሊያቀርቡላቸው ወደቤታቸው ሄዱ። አንደኛው «አንቺ ሴት በእጄ አንዲት ወፍ ይዣለሁ። ይህቺ ወፍ በህይወት መኖር አለመኖሯን ንገሪኝ» ብሎ ይጠይቃቸዋል። ብልኋ ሴት መልስ ከመስጠታቸው በፊት ለረጅም ጊዜ ዝም ብለው በስተመጨረሻ እንዲህ አሉ። «አንተ የያዝካት ወፍ በህይወት ትኑር አትኑር አላውቅም። ግን የማውቀው በአሁኑ ጊዜ በአንተ እጅ ውስጥ መሆኗን ነው። በእጅህ ውስጥ ነው ያለችው» ብለው መለሱለት።

የእኚህ ባልቴት መልስ ሲተረጐም «ይህቺ ወፍ ሞታ ከሆነ በዚያ አይነት አግኝተሃታል ማለት ነው። ካልሆነም ገድለሃታል። በህይወትም ካለች ልትገድላት ትችላለህ ማለት ነው። እንድትኖር ወይም እንድትሞት የምትወስነው አንተ ነህ። በየትኛውም መንገድ ቢታይ ወፏ በህይወት እንድትኖር ወይም እንድትሞት ኃላፊነቱ የአንተ ይሆናል» የሚል ነው። ኢትዮጵያን በምለቅበት ጊዜ ሁላችሁም አንዲት ወፍ

በእጃችሁ ይዛችኋል። ይህቸም ወፍ ህይወት አላት። ወፏም የዲሞክራሲ ተምሳሌት ናት። ይህችን ወፍ በህይወት ልታቆይዋት እንደምትችሉ እምነቴ በእናንተ ላይ የፀና ነው። እንግዲህ ልብ በሉ! አብራችሁ ሆናችሁ እጅግ ያማረ ነገር ሰርታችኋል። ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ፓርላማ ገብተው ህገ መንግስቱ በሚፈቅደው አይነት የመንግስት ተሳታፊ ሆነው ይሠራሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። እንደዚህ ከሆነ ሁላችንም በጐ ፍፃሜውን እናያለን።

እኒህ አፍሪካዊ ፀሐፊ ቶኒ ሞሪስን ስለ ወደፊቱ ጊዜም ተናግረዋል። እሳቸው ይህን ለመግለፅ የሞከሩት ህዝቡ ባለፈው ላይ ይበልጥ እንዳተኮረና ስለወደፊቱ ምንም አይነት ፍላጐት እንዳላሳየ አድርገው ነው። ወደፊት ማየት ስንል ለምሳሌ ስለ 3000 ወይም ስለ 4000 ዓ.ም ማሰብ ወይም መገመት እንችላለን? የሚለውን ያካትታል። ያሳለፍናቸው ዘመናት እየረዘሙ ሄደዋል። በብዙዎች እይታ የወደፊቱ ዘመን የሚተንና ተስፋ የማይጣልበት ሆኖ እየቀረበ ነው። ሞሪሰን የሚሉን ወደኋላ የሚጐትቱንን ሁሉ ጥለን ካለፈው ታሪካችን በጐ በጐውን እንውሰድ ነው። እነዚህም ነፃነት፣ ደግነት፣ ጥልቅ የፖለቲካ ግንዛቤ፣ ኃላፊነትን የሚጋራ ህብረተሰብን የሚያካትቱ ናቸው። እነዚህን በጐ ገፅታዎች በመውሰድ የወደፊቱን ዘመን የተሻለና ብሩህ ማድረግ ይቻላል።

በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ የዜና አውታሮች የወደፊቱ ዘመን ጨለማ እንደሆነ ይናገራሉ። ለምን እንደዚህ ይሆናል? እኔ የማምነው በኢትዮጵያ ሁለት አይነት አጋጣሚዎች ይኖራሉ ብዬ ነው። አንደኛውን ከማንነት ጋር የተጣመረ ፖለቲካ (Identity Politics) ብዬ እጠራዋለሁ። ሁለተኛውን ደግሞ የኢንተርኔት ፖለቲካ (Internet Politics) እለዋለሁ።

ከማንነት ጋር የተቆራኘ ፖለቲካ የምለው ባለፈው አመት በአሜሪካ ውስጥ የተፈጠረው አይነት ነው። ይህም መራጩ ህዝብ እንዲመርጥ የሚቀርቡለት ሰፋ ያሉ ሀገራዊ ጉዳዮችና መርሆች ሳይሆኑ እጩ ወይም ፓርቲው የሚያቀርባቸው ጠባብ ነጥቦች ናቸው። በኢትዮጵያ ሁኔታ የኢንተርኔት ፖለቲካ የሚባለው በውጭ ሀገር በሚኖሩ፣ በሀይል በሚጮሁና በአደገኛ ጥላቻ ላይ የተመሠረተ የጥቂቶች ቅስቀሳ ነው። አብዛኞዎቹ በዚህ ሀገር ውስጥ ለረጅም ጊዜያት ምን አልባትም በአስርት ከሚቆጠሩ አመታት በላይ አልነበሩም። ፍላጐታቸው በሀገር ቤት ካሉ ኢትዮጵያዊያን ያነሰ ነው ሊባል ይቻላል። እዚህ ያሉት ኢትዮጵያዊያን ቀድሞ በነበረችዋ የኢትዮጵያ መልክና በጐሳ ልዩነት እንዲነሳሱ ይፈልጋሉ።

ይህን ከፈቀድን ባለፈ ታሪክ የሚያመልኩ የበላይነቱን ይይዛሉ። የወደፊቱን ሁኔታም ጠርገው በመግፋት ህብረተሰቡን ወደ ንትርክ /ብጥብጥ/ ሊከቱት ይችላሉ። በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ ኢትዮጵያዊያን እ.ኤ.አ 1974 ወይም 1991 ወይም 2000 ላይ በነበረው የፖለቲካ ስልት ላይ ተቸክለው የቀሩ ናቸው። እነዚህ ሰዎች ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሀገሪቱ ውስጥ ምንም አይነት በጐ ለውጥ አልታየም ብለው ያምናሉ። እነዚህ በአሁኑ ጊዜ በግልፅ የሚታየውን ለውጥ ለመቅበር የሚፈልጉና አበረታች ተስፋንም የሚያጨልሙ ናቸው።

በአሁኑ ጊዜ የሚታዩት ዋና ዋና አበረታች ነጥቦች የመድብለ ፓርቲ መኖር፣ ህገ መንግስትና ህጋዊ ተቋማት መቋቋማቸውና በዚህም ላይ በመመስረት ውይይትን ለማከናወን መቻሉ ይጠቀሳል። እነዚህ ለውጥ በተለይም የኢኮኖሚ መሻሻል እንዲመጣ የሚያግዙ ናቸው። በእኔ በኩል ሀገሪቱ በአለም አቀፉ ኢኮኖሚ እንድትታቀፍ ለውጡ መፋጠን አለበት እላለሁ። ጠንካራ የኘሬስ ውጤትና ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት መጠናከር አለበት። ይህን መብት በቅርብ ጊዜ እንደሚሻሻል ተስፋ አደርጋለሁ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለጠ ቅላላው ህብረተሰብ እድገት የሚያግዝ የልማት አጀንዳም መነደፍ ይኖርበታል። እነዚህ አበረታች ገፅታዎች እስከመጨረሻው ከቀጠሉ የተሻለና ብሩህ ተስፋ እንዲሁም ብሔራዊ ተሀድሶ ይኖራል።

ይህ እንዴት ተግባራዊ ሊሆን ይችላል? የሚል ጥያቄ ቢነሳ ቀደም ባሉት ጊዜያት የነበሩትን በህብረት የማደግን ነባር አስተሳሰብ ፣ በታሪክና በሌላም አለም ጠቃሚነታቸው የተረጋገጠላቸውን ነባር ልምዶች እንደገና እንዲታደሱ በማድረግ ነው። ሁሉንም በማካተት ፣ አፍራሾችን፣ የዘር ጥላቻን፣ ከአንዱ ወይም ከሌላኛው ጋር መፈረጅን፣ ከራስ ሃሣብና እምነት በስተቀር የሌላውን ሃሳብ አሳንሶ ማየትን ማስወገድ ያስፈልጋል።

ከ80 በላይ ልዩ ልዩ ጐሳዎች ባሉባት ኢትዮጵያ በተሰወነ መልኩ የጐሣዎች መቀናቀን ቢኖር ሊያስገርመን አይገባም። ነገር ግን አሁን ያለን የእውቀት ደረጃ እንደሚያመለክተው ከዚህ መቀናቀን

ተነስቶ ወደ ጥላቻ ከተሸጋገረ የጐሣው ፍጥጫ አደገኛ መልክ ሊይዝ ይችላል፡፡ በመሆኑም ዛሬ ከምንጊዜውም በላይ መቻቻል እንዲኖር ጥሪዬን አቀርባለሁ፤ መቻቻል የጐሣ ፍጥጫን ለማርከስ ብቸኛው መንገድ ነውና፡፡

በኢትዮጵያ ብዙ ህዝብና ቡድኖች አሉ፡፡ በአሜሪካና በሌላውም አለም በተመሳሳይ በራሳቸው መንገድ የሚሄዱ ሌላውንም ነጥለው የሚመለከቱ ቡድኖች አሉ፡፡ ለእኛ ወጣቶች አንድ ነገር ማስታወስ እፈልጋለሁ፡፡ ይህም አብረን ለመኖር እርስ በርስ መፋቀር ሳይሆን እርስ በርስ መከባበር ቀዳሚ መሆኑን ነው፡፡ እርስ በርስ በመግባባት በሰላምና በመጣጣም አብሮ መኖር ይቻላል፡፡ ይህ መቻቻልን ተግባራዊ ማድረግ እንዳለብን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ አይነት ልንቀርፀው የሚገባን ራዕይ በኢትዮጵያ፣ በአሜሪካ ወይም በተቀረው አለም የተለያዩ ባህሎችን የሚያጋራ ህብረተሰብ ለመፍጠር አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ ይህ ራዕይ ግቡ የተለያዩ ባህሎችን የሚጋራ ግለሰብ ለመፍጠር መሆን አለበት፡፡ በዚህ ራዕይ መሠረት አንድ ግለሰብ ሀገሪቱ ከዘመን ወደ ዘመን ያሸጋገረችለትን ቅርስ እኩል ዋጋ መስጠት አለበት ማለት ነው፡፡

ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ የዲሞክራሲ መሰረቷን ለማጠንከር ዜጐቿ ትርጉም ያለው መልካም አስተዳዳር ለመመስረት እንዲሳተፉ ለማድረግ ራሷን የምትመረምርበት ወሳኝ ወቅት ላይ ትገኛለች፡፡ እኔ የተማርኩበት አልማ ማተር ስፔልማን ኮሌጅ የቀድሞ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ጆኔታ ኮል «እኛ ልዩነት ነን፣ ልዩነትን እንፈቅዳለን፣ ልዩነትን ለመረዳት እንማራለን፣ ልዩነት በፍፁም ሌላ ልዩነት እስካላመጣ ድረስ ልዩነትን እናከብራለን» ብለው ነበር፡፡ እንደማስበው በእናንተ እገዛ ኢትዮጵያ እዚህ ደረጃ ላይ መድረስ ትችላለች፡፡

ንግግሬን የጀመርኩት በመዝሙር ነው፡፡ በመሆኑም ንግግሬን በአንድ ሌላ አፍሪካ አሜሪካዊ መዝሙር እንድቋጭ ይፈቀድልኝ፡፡ ይህ መዝሙር ኢትዮጵያና ህዝቦቿ ወደፊት እንዲገሰግሱ ያለኝን ተስፋ የሚያንፀባርቅልኝ ነው፡፡ ለእኔ ይህ ግጥም እንደ ፀሎትም ያገለግለኛል፡፡

«በድካማችን ጊዜ አምላክ ይረዳናል
የሚፈሰው እንባችንም በእርሱ ይታበሳል
ረጅሙን ጐዳና መርተህ እዚህ አደረስከን
በማይሻረው ስልጣንህ
ብርሃን አሳየኸን
ለዘላለም በዚሁ ጐዳና መራመድ እንችል ዘንድ እንፀልያለን፡፡
ወደአንተ እንመጣ ዘንድ መንገዱን ምራን
ልባችን በአለም የወይን ጠጅ ሰክሮ እንዳይረሳህ እርዳን
በማይለካው ሃያል ክንድህ
ለዘላለም ፀንተን እንድንቆም
ለአምላካችን እውነተኛ
ለትውልድ ሀገራችን ሀቀኛ አድርገን፡፡ »

እሄዳለሁ፣ የፍፃሜውን ለማየትም እጓዛለሁ፡፡ እናንተም እንደእኔው ፍፃሜውን ለማየት ትጓዛለችሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ከሁሉም በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ያሳለፍኩት ትዝታዬን በቀሪው ዕድሜዬ እንደማልዘነጋ ልገልፅላችሁ እወዳለሁ፡፡

አመሰግናለሁ፡፡